# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ቛፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 21 መስከረም 29 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ !
አባዝተው
ያሰራጩ !

## የመለስ ዜናዊ ዘረኛና አምባገነን ቡድን ማንንም በፀረ-ኢትዮጵያነት የመክሰስ የሞራል ብቃት የለውም።

በቅርቡ ታትሞ በወጣው ሪፖርተር በሚባል የወያኔ/ኢህአዴግ ጋዜጣ ላይ፣ የአሜሪካው ኮንግረስ አባል ዶናልድ ፔይን፤ ባራክ ኦባማ በምርጫ ካሸነፉ አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት እንደገና እንደምታጤንና መንግሥታትም በፀረ ሽብርተኝነት ትግል ስም አሜሪካን የሚያሞኙበት ጊዜ ያበቃል ሲሉ በመናገራቸው። የመለስ ዜናዊ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር "ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ይዘዋል" ስለሚላቸው የሚስተር ፔይን ሲያብራራ "ሚስተር ፔይን የእውነት ሰው ቢሆኑና ለሰብዓዊ መብትና ዴሞክራሲ መስፈን የሚጨነቁ ቢሆኑ በኤርትራ ተገኝተው እውነታውን ካዩ በኋላ በኤርትራ ላይ አስተያየት በሰጡ ነበር። የሚል ጽሁፍ ማየቴ በጣም አስገረመኝ።

ዶናልድ ፔን ከክርስቶፎር ስሚዝ ጋር በመሆን HR 2003 የኢትዮጵያ የሰብዕአዊ እና የዴሞክራሲ ቢል ተብሎ የሚታወቀውን የህግ ረቂቅ ለአሜሪካ ምክር ቤት ያቀረቡት፣ ከግንቦት ምርጫ 97 በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በመጓዝ የተለያዩ የመንግስት አካላትን፣ በጊዜው በእስር የነበሩትን የቅንጅት መሪዎችን ከአነጋገሩና፣ በሀገሩ ውስጥ የሰፈነውን ከፍተኛ አፈና ከተመለከቱ በኋላ ነበር። በጊዜው ዶናልድ ፔንን አዲስ አበባ በአረፋበት ሆቴል ለጥቂት ደቂቃዎች ለማናገር እድል ለአገኘ አንድ የሀገረ ወስጥ ጋዜጠኛ "እነዚህ ሰዎች እኔንም ሳያስሩኝ ከእዚህ ብሄድ ያሻለኛል" ብለውት እንደነበር ውስጥ አዋቂዎች በወቅቱ ሰምተውታል።

በመሰረቱ የህግ ሪቂቁ ለምን ኢትዮጵያ ላይ አነጣጠረ የሚለው የደንቆሮች ዘፈን የሳተው ነገር ረቂቁ ያነጣጠረው ኢትዮጵያ ላይ አለመሆኑን። ያነጣጠረው የአሜሪካ ታክስ ከፋይ በእርዳታ ስም ለውጭ ሃገሮች የሚሰጠው ገንዘብ በምን መስፈርቶች ላይ ይሁን የሚል ነው። ኢትዮጵያ እዚያ ውስጥ የገባችው የአሜሪካ ታክስ ከፋይ በአመት ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ በምጽዋት ለአገዛዙ ስለሚለግስ ብቻ ነው። ኤርትራም ይሁን ሌላ ሃገር ረቂቅ ህጉ ያልተመለከተው ኤርትራ ከአሜሪካ እንደ ኢትዮጵያ የምትመጸወተው ነገር ስለሌ ነው። ህገ-ረቂቁ የሚለው ገንዘባችን ከፈለጋችሁ፣ ሰው አትግደሉ፣ በፍትህ አታላግጡ፣ ምርጫ አታጭበርብሩ ወዘተ። አይ በእዚሁ እንቀጥላልን ካላችሁ ገንዘብ አንሰጥም፣ ገዳዮች ወደ ሃገራችን ለስራም ሆነ ለጉብኝት እንዲመጡ አንፈቅድም ነው የሚለው። ረቂቅ ህጉ ያነጣጠረው በኢትዮጵያ ላይ ሳይሆን በምኒሊክ ቤተመንግስት አድፍጦ ኢትዮጵያውያንን በሚበላ መለስ በሚባል የአውሬዎች ቁንጮ ላይ ነው። ምጽዋት ከፈለግህ፣ የኢትዮጵያውያንን ደም አታፍስ ነው የሚለው። ታዲያ ከአሜሪካ ምጽዋት የማትቀበለው ኤርትራ ላይ ዶናልድ ፔን ለምን አልጮሁም የሚለው የውጭ ጉዳይ ባለስልጣናቱ ኡኡታ ምን አመጣው። ሰዎቹ ደንቆሮዎች ናቸው ያልኩት ያለምክንያት አይደለም።

ሌላው በዶናልድ ፔን ላይ መለስና ኩባንያው የሚያነሳው ክስ ሰውየው ጸረ-ኢትዮጵያዊ ነው የሚል ነው። ተው ጃል እረባካችሁ፣ እረ እፈሩ እናንተም አፍ አውጥታችሁ ሌላውን በጸረ-ኢትዮጵያዊነት ትከሱ!! ያውም ግድያ አቁሙ ያላችሁን፣ የተጠቃን ህዝብ ጠበቃ፤ መቼም የፈረደበት ህዝብ ስለ ዶናልድ ፔን ማንነት ከእናንተ ራደዮ ውጭ የሚነግረው የለም ብላችሁ ይሆናል። የግንቦት 7 ድምጽ ጉድ እያረጋችሁ ነው። የመለስ ጀሌዎች ዶናልድ ፔን ማን እንደሆነ ሳያውቁ ቀርቶ አይደለም። የደቡብ አፍሪካ ህዝብ መብት እንዲከበር በወጣትነት እድሜው በአሜሪካን ውስጥ ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ እያዘጋጀ ከደቡብ አፍሪካ ኤምባሲ አልወጣም እያለ እጁን ወደ ኋላ እየተጠመዘዘ ታሰሮ ሲወሰድ በምስል የተደገፋ በርካታ የታሪክ ማስረጃ ስላለው የመብት ጠበቃ ዶናልድ ፔን እኮ ነው የምታወሩት። ያገራችን ህዝብ አያውቅም ብላችሁ ነው። ጸረ ኢትዮጵያዊ አላችሁት ። ይሉኝታ ቢሶች። ህዝባችን ስለእናንተ የማያውቀው ጉድ የለም። እንዳው እናንተ ሰትሰሙት ደስ ስለሚለው ልድገምለት።

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

**ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ**

**በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም**

**ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2:00 እስከ 2:30 ፤ በ17655 ኪሎ ኸርዝ በ16 ሜትር ባንድ ወይም በ21555 ኪሎ ኸርዝ በ13 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰራጨውን የሬዲዮ ፕሮግራም ይከታተሉ።**

## የአገዛዝ ስርአቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት አለቆቻቸውን ለህዝብ መክሰስ ጀመሩ

የመለስ አገዛዝ የሃገሪቱን የትምህርት የጥራት ደረጃ እየገደለ፣ የአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች ከአስረኛ ክፍል በላይ መማር የሚችሉበትን እድል ዘግቶ ባለበት ሁኔታ መለስና ጥቂት አደግዳጊዎቹ ልጆቻቸውን በአውሮፓና በአሜሪካ ኮሌጆች በአመት ከ30 .000 እስከ 40.0000 የአሜሪካ ዶላር እየከፈሉ የሚየስተምሩ መሆኑን በስርአቱ ውስጥ ከፍተኛ ሰልጣን እንዳላቸው በመግለጽ ለግንቦት 7 የኢሜል ደብዳቤያቸውን የላኩት ግለሰብ አጋላጡ።

የመለስ ዜናዊና ልጆችና የተፈራ ዋልዋን የእንጀራ ልጆች ስምና እንዲሁም በእንግሊዝና በአሜሪካ ሃገር የሚማሩባቸውን ኮሌጆች ስም በመዘርዘር፣ የሚጀምርው የባለስልጣኑ ኤሌክትሮኒክ ደብዳቤ ላይ ግለሰቡ፣

በእነዚህ ኮሌጆች ለመማርና- ልጆቹን በእነዚህ ሃገሮች ለማኖር የሚወጣውን ወጪ ደምረው በአንድ ልጅ ከ30ሽህ እስከ 40 ሽህ የአሜሪካ ዶላር ወጪ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

እኚሁ ባለስልጣን ይላሉ፣

አንዳንዶቻችን ከፍተኛ ስልጣን ቦታ በንቀመጥም እንደመለስና እንደአናዳንዶቹ የስርአቱ በላስልጣናት በሃገር ውስጥ ይሁን በሃገር ውጭ ምንም ሃብት ያላከበትን፣ ልጆቻችን እንኳን በውጭ ሃገር ቀርቶ መሃከለኛ ገቢ ያለው የሃገራችን ነጋዴ ልጆቹን ከሚያስተምርበት የግል ትምህርት ቤት አስገብተን ማስተማር ያልቻልን ነን።

የኢትዮጵያ ህዝብም፣ በውጭ የሚገኘውም ኢትዮጵያዊ፣ የእናንተም ራዴዮና ጋዜጣ ጭምር ግን ሃገሩን የሚዘርፋት በያዙት ስልጣን ዲታ እየሆኑ ያሉት በውጭ ሃገሮች ብር የሚያስቀምጡት፣ ቤት የሚገዙት ሁሉም ከፍተኛ የኢህአዴግ ባላስጣልናት እንደሆኑ አድርጎ ማየቱ ቤታችንና ጉዋዳችንን ለምናውቀው ለእኛ ለባለጉዳዮቹ ሃዘን ፈጥሮብናል ብለዋል።

እኒሁ ባለስልጣን በላኩት ኢሜል እንዳሉት፣ ከምኒስትሮችም ሆነ ከጦር መኮንነኖቹ መሃል እነማን ቢጠሯቸው የማይሰሙ ዲታዎች እንደሆኑ ለማወቅ የሚጠይቀው ቀላል ጥናት እንደሆነ እየታወቀ በጅምላ የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስጣናት የሆነው ሁሉ እንደነመለስና እንደነተፈራ ዋልዋ ልጆቹን ውጭ እየላከ ለደህንነታቸው ሳይቀር ለሴኩሪቲ ከፍተኛ ወጪ እያወጣ ልጆቹን የሚያስተምረው፣ ወይም እንደሌሎቹ ባለስልጣናት ምርጥ የከተማውን መሬት ወስዶ በሙስና በተሰባሰበ ሃብት ጉድ የሚያሰኙ ቪላዎች ሰርቶ በውጭ ምንዛሪ እስከ 10ሽ ደላር የቤት ኪራይ ከአንድ ቤት በወር የሚሰበስበው፣ ስሙን እየደበቀ ከነጋዴ ጋር እየተመሳጠረ በወንድሙ፣ በእህቱ፣ በሚስት ስም ትላልቅ የንግድ ኢምፓየር የሚዘረጋው ሁሉም የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣን እንደሆነ አድርጎ የሃገራችን ህዝብ ማሰቡ ያሳዝነናል ብለዋል።

**በአሜሪካን ዜግነት ያለው ኢትዮጵያዊ ያውቃሉ?**

**ልጅ፣ ወንድም፣ አህት፣ የቅርብ ዘመድ፣ ጓደኛ ሊኖሮዎት ይችላል።**

**በፍጥነት ብእርዎን ወይም ስልክዎን ያንሱ ወይም ኮምፒተርዎን ያስነሱ።**

**መልእክት ይላኩ። የዘንድሮ የአሜሪካን ምርጫ የእኛንም ሃገር ይመለከታል ይበሉ።**

**በአሜሪካ የምትገኙ ወገኖቼ ውጡና ለምርጫ ተመዝገቡ። ኦባማን ምረጡ ይበሉ።**

**ፕሬዚደንት ከሆንኩ ህዝባቸውን ከሚያሸብሩ አምባገነኖች ጋር አሜሪካ ወዳጅነት አይኖራትም ብለዋል ኦባማ።**

**መለስ ዜናዊን አይነቶቹን አምባገኖች ማለታቸው ነው።**

**ኦባማን ማስመረጥ በመለስ ዜናዊ ላይ የሚገኝ የዲፕሎማሲ ድል ነው። ለነጻነትና ለዴሞክራሲ እኛው በእኛው የምናደርገውን ትግል ባይተካም፣አጋዥ ነው።**

# ርእሰ አንቀጽ

## የመለስ ወረራ በሱማሌ ከሽንፈት ወደ ማፈግፈግ

አሜሪካ ዜጎቿን ከባይዶዋ ለማስወጣት በተጠንቀቅ ላይ ናት ። የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ በነ መለስ የሃዋሳ ጉባኤ ላይ ዋና ተሳታፊ ሆነ ። የኪስማዩ ከተማ አውሮፕላን ጣቢያ በኢማም አህመድ ጉሬ ወይም በዘወትር አጠራሩ "ግራኝ አህመድ" ስም ተሰየመ ። የሱማሌ ክልል ፕሬዚደንት አብዱላሂ ሐሰን ተባረረ ። ልደቱ አያሌው ብዙ የኢትዮጵያ ወታደሮች ደማቸው በከንቱ የፈሰሰበትን ወረራ በደገፈበት አፉ፤ "የኢትዮጵያ ሠራዊት ከሱማሌ እንዲወጣ እንዲጠይቅ መመሪያ ከቤተመንግስት ተላከለት" ። ባራክ ኦባማ በአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ አሸናፊ ኮከባቸው ማብራት ጀምራለች ። የአሜሪካ ኢኮኖሚ ቀውስ ወደ አውሮፓም እየተዛመተ ነው ወዘተ የሚሉ ዜናዎች የሰሞኑን የዜና ገፆች ያጣበቡ ናቸው ። እነዚህ ተናጠል ክስተቶች ምን አገጣጠማቸውና ነው፤ ልደቱን ከኦባማ፤ የቻይና ኮሚኒሰት ፓርቲን ከአሜሪካ ቀውስ ጋር እኩል የሚያሰልፈው ትሉ ይሆናል ። እውነትም ነገሩ ግር የሚል ነው ። ቁምነገሩ ግን እነዚህ ሁሉ ተናጠል የሚመስሉ ክስተቶች የሚያነጣጥሩት የመለስ እህል ውሃ በሱማሌ ውስጥ እያለቀ መሆኑን ነው ።

መለስ በወትሮአዊ ብልጣብልጥ ስሌቱ "የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በኦባማ አሸናፊነት የሚጠናቀቅ ከሆነ ፤'ይህ ጦሬን ከኢራቅ አስወጣለሁ' በሚል መፈክር ስር የተወዳደረ ሰው ፤ ለሱማሌ ወረራችን ከቡሽ አስተዳደር ድብቅ በጀት የሚደጎመንን የቅጥረኝነት ደሞዝ እንዲቋረጥብን ያደርግ ይሆናል" ብሎ መለስ ተጨንቋል። በዚህ ላይ ሱማሌ ውስጥ ከሸባብ ወጣቶች በየእለቱ የሚደርስበትን ሽንፈት መደበቅ ከማይችልበት ደረጃ ደርሷል ። የሱማሌ ወጣቶች ፀረ-መለስ ወረራ ተጋድሎ ፤ ከደረሰበት ሽንፈት አገግሞ ፤ መለስን ጭራውን ቆልፎ የሚወጣበት ድክመት ላይ አድርሶታል ። የሸባብ ወጣት አርበኞችን ምትሃታዊ ጥቃት መቋቋም ያቃተውም የመለስ ወራሪ ጭፍራ ፣ በሰላማዊ ህፃናትና አረጋውያን ላይ የሚያደርሰው ግፍና እልቂት በአስር እጅ በመጨመር ላይ ይገኛል ። ግፉም በሞቃዲሾ ላይ ሳይገታ ፤ ወደሃገራችንም ድንበር ዘልቆ በመግባት፤ መለስ በኦጋዴን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ አሰቃቂ ጭፍጨፋ በማድረግ ላይ ይገኛል ። ይህንንም ጭፍጨፋ አሜን ብለው መቀበል ያቃታቸው ክልሉን የሚያስተዳድረው "የሱማሌ ህዝብ ዴሞክራቲክ ፓርቲ" አባላትና መሪዎች በመመንጠር ላይ ሲሆኑ ፤ ክልሉን በአስቸኳይ አዋጅ ስም በመለስ ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር ለማድረግ ውጥኖች እንዳሉም ይሰማል ። በሱማሌ የተካሄደው ጭፍጨፋ በዘር ማጥፋት ወንጀል ያስጠይቃል የሚሉ የምዕራብ የህግ ጠበቆችም ድምፃቸው እየጨመረ ነው ።

በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች መለስ ሱማሌን በእብሪትና ጭፍጨፋ ወርሮ መያዝ ከማይችልበት ደረጃ ደርሶአል ። ተሸንፎ መውጣቱም የጊዜ ጉዳይ እንጂ አይቀሬ ነው ። የሚያሳዝነው "ጦራችሁን ከባይዶዋ አስወጡ እንጂ ከእናንተ ጋር በጠላትነት ለመሰለፍ ፈቃደኛ አይደለንም" ይል የነበረው የሻሪያ ፍርድቤቶች ምክርቤት በመለስ እብሪት ፈርሶና ተጨፍጭፎ በምትኩ እጅግ አክራሪ የሆነ የሸባብ ወጣቶች ንቅናቄ የበላይነት መያዙ ነው ። የቅጥረኛው መለስ እርምጃ ለአመታት የማይበርድ የሱማሌ ወጣቶችን ምሬትና ጠላትነት እንዳተረፈልን ስናይ ሃዘን ይሰማናል ። ሀዘን ብቻ ግን በቂ አይደለም ። የመለስን ወረራ እያወገዝን፡ የኦጋዴን ወገኖቻችንን የሚጨፈጭፉ ወንጀለኞችን በዘር ማጥፋት ወንጀል እየተፋረድን፡ በሱማሌ ላወደምነው ንብረትና ህይወት ካሳ እየከፈልን፡ የተበላሸውን መልካም ጉርብትናችንን መልሰን የምንገነባበት ቀን ሩቅ እንደማይሆን ፅኑ ተስፋ አለን። ከተስፋችን ጋርም፤ ጎን ለጎን የሶማሊያ ወጣቶች እብሪተኞቹ እነ መለስ በፈጸሙት ወረራ ተበሳጭተው፤ ኢትዮጵያውያን በበጎ ዐይን ከማያዩዋቸው ሀይሎች ጋር እንዳይወዳጁ "የግንቦት ሰባት ንቅናቄ"

### የአገዛዙ ባለስልጣናት ከገጽ 1 የዞረ

ሆኖም ግን በአመራሩ ውስጥ የምንገኝ በሲቪል ይሁን በወታደራዊ መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ ከፍተኛ ሰልጣን ያለን እንደማንኛው የሃገሪቱ ህዝብ በወር ከሚከፈለን ደምወዝ በላይ ገቢ የሌለን፣ ልጆቻችን በመንግስት እንደማንኛውም ወገናችን ልጆች የትምህርት ደረጃው በወደቁ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ፣ ያረጀ ጫማቸውን እያየን መቀየሪያ መግዣ አጥተን እንዳለየ የምናልፈው፤ አንዳንዶቻችን ልጆቻችን የአስረኛ ክፍል ፈተና ወድቀውብን የምናደርጋቸው የጠፋብን፣ ከሌላው ህዝብ በተሻለ ከምናገኘው ደሞዝና ከስልጣናችን ጋር ከመንግሰት ከተፈቀደልን ጥቅሞች ተጨምሮ በኑሮ ውድነት ከወር ወር ለመድረስ ትግል የሆነብን በርካታ ባለስልጣናት እንዳለን ይታወቅልን። ይህን መልእክት ለህዝብ ባተደርሱልን ብለዋል እኝሁ ባለስልጣን፣ መልእክታቸውን ሲያጠናቅቁ አባቶቻችን ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ ተብሏል ምን ይደረጋል ብለዋል።

ግንቦት ሰባት ሬዲዮ የዝግጅት ክፍል ግለሰቡ በደብዳቤቸው የጠቀሷቸውን የባለስልጣኖቹን ስምና የሚማሩበትን ኮሌጆች ትክክለኛነት ካረጋገጠ በኋላ ልጆች ከነፈሰ ገዳይ ይሁን ከዘራፊ ለመወለድና ላለመወለድ ምርጫ ስለሌላቸው በአባቶቻቸው ሃጥያት ምንም አይነት ችግር ውስጥ መውደቅ አለባቸው ብሎ ስለማያምን የልጆቹን ስምና የሚማሩባቸውን ኮሌጆች ይፋ ከማድረግ ተቆጥበናል።

### ከገጽ1 የዞረ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ

ዛሬ በሐገራችን በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተፈናጦ የሚገኘው በመለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኛ አምባገነን ቡድን፣ ገና ከውልደቱ ጀምሮ የቆመበት መሰረት ዘረኛነት በመሆኑ፣ ምንም ሐገራዊ ጉዳይ የሚያሳስበው አለመሆኑን በተለያዩ ጊዚያት በወሰዳቸው ብሄራዊ ደህንነትንና ጥቅምን የመሸጥ ውሳኔዎቹ በበቂ ሁኔታ አስመስክሯል።

በተለይ ለሥልጣን በበቃበት ጊዜና ከዚያም በኋላ፣ የዚህ ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ በአደባባይ፣

"የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚባል ሕዝብ የለም፣ የተለያዩ የዘውግ ማሕበረሰባት እንጂ፣

የኢትዮጵያ እድሜና ታሪኳ ከመቶ አመት አይበልጥም፣ እሱም ቢሆን የአንድ አካባቢ ታሪክ ነው፣

ለእኛ ባንዲራው ጨርቅ ነው፣ ለወላይታው የአክሱም ሀውልት ምኑ ነው፣
የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ የሚያስጨንቀን ጉዳይ አይደለም፣

ለሱዳን የሰጠነው መሬት የለም ቢኖርም፣ ሱዳኖች ከእኛ በተሻለ መሬቱን ሊያለሙት ይችላሉ፣

እዚህ የመጣነው ኢትዮጵያዊነትን ለመሞከር ነው፣ ካልተስማማን ደግሞ በህገ መንግስቱ ያስቀመጥነውን መብት ተጠቅመን ጥለን እንሄዳለን"፣ ሲል የተደመጠው በአጋጣሚ ሳይሆን፣ ዘረኝነት ያሸማቀቀው ስብዕና፣ ሐገር፣ ታሪክ እና ሕዝብ ያላቸውን ግንኙነት፣ የሚያይበትን ዓይን ምን ያህል ያንሸዋረረው እንደሆነ የሚይሣዩ ተጨባጭ መረጃዎች ናቸው። ታዲያ በመለስና በጓደኞቹ አይምሮ ሲሰላ ፀር ኢትዮጵያነት፣ ምን ማለት ይሆን?

የመለስ ዜናዊ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ዶንልድ ፔን ፀረ ኢትዮጵያ አጀንዳ ያራምዳሉ ብሎ ላለበት ጉዳይ የሰጠው ምክንያት ኤርትራ ሄደው ሲመለሱ ስለ ኤርትራ መንግስት ላይ ምንም አይነት ወቀሳ ባለመሰንዘራቸው ነው።

እዚህ ላይ የመለስ ዜናዊ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በዶናልድ ፔን ላይ የጸረ ኢትዮጵያዊነት ክሱንና የኤርትራን መንግሰት ቀላቅሎ ሲያቀረብ ጌታውን መለስ ዜናዊን ለጥቃት እያጋለጠ እንደሆነ አለመረዳቱ ነው። ወይም ለሃገራችን ህዝብ ትልቅ ንቀት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መስጠቱን ነው። አንድ የሳተው መሰረታዊ ጉዳይ ቢኖር፣ የኤርትራ ሕዝብ መብት ኖረውም አልኖረውም፣ በኤርትራ መግስትን የሚመራው አካል መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያዊነቱ እንደሚያፍረው በኤርትራነቱ የማያፍር ነው። በአደባባይ በኤርትራዊነቱ ሲሸማቀቅና በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኤርትራዊነትን ሊያንኳስስ ሲሞክር ታይቶ አይታወቅም። መሪዎቹም የሚኖሩት በኤርትራ ሕዝብ መሀል ነው እንጅ፣ እንደ መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ እራሳቸውን እንደ ወራሪ፣ የሀገሩን ሕዝብ እንደ ተወራሪ እያዩ ከእዚህ በፊት በታሪክ ከምናውቃቸው የጣሊያን ወራሪ ፋሽስት መሪዎች ከሚደረግላቸው ወታደራዊ ጥበቃ በላይ እየተጠበቁ አይደለም።

ቀደም ብዬ ለምን እረቂቁ ህግ ኢትዮጵያን ብቻ ይመለከታል ብዬ ከጠቀስኩት ዋና ምክንያት በተጨማሪ ዶናልድ ፔን የፖለቲካ ሰው ናችው፣ አዲስ አበባና አሥመራን በጎበኙበት ጊዜ በሁለቱ ሀገር መሪዎችና በሚመሩት ሕዝብ መሀል ያለውን የግንኙነት ልዩነት ማየት ያቅታቸዋል የሚል ግምት የለኝም። ስለ ኤርትራ ብዙም ያላሉት ይህን የመለስና የጓደኞቹን የወራሪነት መንፈስ በሚገባ በማየታቸው ሊሆን ይችላል ብሎ መጠየቅ አይቻልም ይሆን። ኢትዮጵያንና ህዝቧን በወራሪ መንፈስ እየገዛችሁ አታፍሩም፤ በኢትዮጵያ ሰም፤ ኢትዮጵያን ከልቡ ከሚወድ የህዝቧ ታሪክ የጥቁር ዘር ሁሉ መኩሪያ ነው ብሎ ከሚኮራና ከሚያስተምር ታላቅ የኢትዮጵያ ወዳጅ ላይ የጸረ ኢትዮጵያዊ ነውረኛ ክሳችሁን ስትለጥፉ። ማፈሪያዎች።

# ሃይለ ሃሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## የግንቦት7 ደምጽ ራዲዮ ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ጋር ያደረገው ቃለ-ምልልስ የመጨረሻው ክፍል

ጋዜጠኛ ——- በተለይ እርሰዎም ይሁን ዶ/ብርሃኑ ሌሎችም ዛሬ በግንቦት 7 ውስጥ የነበራችሁ ግለሰቦች በአንድ ወቅት ከሰላመዊ ትግል ሌላ ምንም አማራጭ ሊኖር አይችልም ሲል የነበረ ድርጅት አባለት ነበራችሁ። አንዳንዶቻችሁ በተለይ ዶ/ር ብርሃኑ ስለ ሰላማዊ ትግል አማራጭ የለሌው የትግል ስልት ለመሆኑ የተናገሯቸው ንግግሮች በድምጽና በምስል ቀርጸው አንዳንዶች በማስረጃነት ሲያቀርቡ ይታያሉ። እንዴት ከእንዲህ አይነቱ አቋም፣ አመጽን ለመጠቀም ፈቃደኛ እቅድ ያለው ድርጅት መስራቾች ሆናችሁ። አሁንም በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ መታገል ይቻላል ለሚሉት ምን መልስ አላችሁ።

አቶ አንዳርጋቸው —— በቅድሚያ ይህንን ክርክር ከሚያቀርቡት መሃል በርካታዎቹ የመለስ ባለሟሎችም እንደሆነ እንዲታወቅ እፈልጋለሁ። ከሌላው ነገር የበለጠ አስፈጊ ከሆነ አመጽም ለመጠቀም የሚደፍር ድርጅት ከምንም ነገር በላይ የሚፈሩት ስለሆነ። በሰለማዊ መንገድ የእነሱን የህጋዊነት ፈቃድ እየተከተለ የሚሄድን ንቅናቄ እንዳሻቸው መቆጣጠር ማፈን መርገጥ እንደሚችሉ ስለሚያውቁት የመለስ ባለሟሎችና ቅጥረኞች ስለሰላማዊ ትግል ጥሩነት ሊነግሩን ሲዳዳቸው እያየን ነው። እፍረተ-ቢሶች ናቸው። ነገረ ግን ይህ ትችት መለስንም እንቃወማለን ከሚሉ ሃይሎች የሚነሳ ትችት ስለሆነ መልሱን በአግባቡ መስጠት ያስፈልጋል። አዎን በአንድ ወቅት ስለ ሰላማዊ ትግል ጸጋ የሰበከ ድርጅት አባላት ነበርን። ሰላማዊ ትግል ይሰራል አይሰራም በሚባልበት ወቅት ህዝብ በልበ ሙሉነት የተከፈተለትን ጠባብ የዴሞክራሲ ቀዳዳ ተጠቅሞ በአንድነት በጋራ የመለስን የዴሞክራሲያዊነት ጉራ እንዲፈትነው ተግተን ሰርተናል። ስለመለስ መንግስት ምንነት ጥርጣሬ ቢኖረም አንዴ ሰለማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ምርጫ እንግባ ብለን ከወሰንን በኋላ ሰላማዊ ትግል እንደማያሰራ፣ አደጋ እንዳለው፣ ከሰላማዊ ትግል ውጭ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ ሌላ አማራጭ እንዳለ በአደባባይ እየተናገርን ህዝብን ለምርጫ ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲዘጋጅ ማደራጀት የሚቻል አልነበረም። ሰላማዊ ትግል፤ ምርጫ ወዘተ ይስራ አይስራ በሚገባ ለማወቅ አንዴ ከገባህበት፣ ያዋጣል፣ ይሰራል ብለህ ያለህንን እውቀትና አቅም እንዲሰራ ሙከራ ሳታደርግ የግብር ይውጣ ገብተህበት አይሰራም ብትል እራስህንም ሌላውን ማሳምን አትችልም።

ነገር ግን ያለፈውን ትትን ከምርጫው በኋላ የመለስ አገዛዝ የወሰዳቸውን አምባገነናዊ እርምጃዎች ካጤንን በኋላ በእዚህ አገዛዝ ፈቃድ የበላይ ተቆጣጠሪነት፣ በመለስ ህግና በመለስ ህግ አስፈጻሚዎች ቅጥያጣ ፈቃድ ታስሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ትግል ማድረግ አይቻልም ብለናል። በእኛ በኩል ልንነቀፍ የሚገባን ስለአገዛዙ ያለንን አመለካከት፣ በሃገራችን ስለሰፈነው አፋኝ ሁኔታ አስከፊነት ዘርዝረን ስናበቃ ከእዚህ ዝርዝር ትንተና ጋር የማይገናኝ ሊሰራ የማይችል የአደረጃጀት የትግል ስልት ዘዴ ብናቀርብ ነበር። ነቀፋ የሚሰነዝሩት ግለሰቦች ማንሳት ያለባቸው ዛሬ በሃገራችን ላይ በሰፈነው አፋኝ ሁኔታ ውስጥ እንዴት በአጭር ግዜ የኢትዮጵያን ህዝብ የሃገሩ የህይወቱ ጌታ የስልጣን ምንጭ ማድረግ እንደሚችሉ ነው።

ከሰላሳና ከአርባ አመት በኃላ ስለሚመጣ ለውጥ አይደለም እንዲነግሩን የምንፈልገው። ሰላሳና አርባ አመት ለመለስ ዜናዊ ከፈቀድልነት ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር አትኖረንም። ጥያቄው የወቅቱና የዘመኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች አጀንዳ ህዝብን በአፋጣኝ የስልጣን ምንጭ እናድርግ ከሆነ፣ በተለይ አገዛዙ በ2002 በሚጠራው ምርጫ ህዝብ በነጻ የሚደራጅበት፣ ሃሰቡን የሚገልጽበት በነጻ ድምጹን የሚሰጥበት፣ የሚሰጠው ድምጽ በስነስርአት በአግባቡ የሚቆጠርበትን ሁኔታ እንዴት መፍጠር እንደሚችሉ ሊያስረዱን ይገባል። እኛ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ 2002 ሆነ 3002 ህዝብን የስልጣን ባለቤት ማድረግ የሚየስችሉትን የፖለቲካ ነጥቦች፣ የትግል ስልት ታክቲክና ስትራተጂ ፊት ለፊት ሳንሸፋፍን አስቀምጠናል።መደረግ ያለበትን እያደረግን ነው።

ሌላው ያነሳኸው ነጥብ የግንቦት ሰባት አካሄድ ሃገሪቱን ወደ ከፋ ቀውስ ሊወስዳት ነው የሚል ነው። ይህች ሃገር አሁን ካለችበት የከፋ ቀውስ በላይ በአንድ ሃገር ላይ ሊደርስ ይችላል። ይህ አባባል የሚገርም ነው። እስቲ ትንሽ እንደል ፍቀድልኝ።ሰንት ትውልድ እጅግ ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች፣ በከፍተኛ መስዋእትነት በማለፍ ያኖረውን ሃገር፣ ዳርና ድንበር ለባእዳን እየቆረሱ የሚሠጡበት፣ 14 ሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ በጠኔ በሚቃጠልበት፣ ሆን ተብሎ ለሌብነትና ለዘረፋ እንዲያመች ተደርጎ በተቀረጸ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የመጣ የዋጋ ግሽበት ከመቶ ፐርሰንት በላይ ሆኖ፣ ደህና ገቢ አለው የሚባለው ዜጋ ሳይቀር መራብ በጀመረበት ሃገር፣ ከካፍሎ ለመግዛት እንዲያመች መርዘም የሆነ የዘረኛነት መርዙን የሚያስፋፋ አገዛዝ በነገሰበት፣ ዜጎችን መንደራቸውን እያቃጠሉ እናትና እህቶቻችንን በልጆችና በባሎቻቸው ፊት እየደፈሩ፣ ወንዶቹን በቀጭን ሽቦ ከዛፍ ላይ እየሰቀሉ መኖሪያ መንደራቸውን እያቃጠሉ ረሃብን ለዘር ማጥፊያ ወንጀላቸው የሚጠቀሙ ገደዮች በነገሱበት ሃገር፤ እስቲ በሶማሊያ የሚሆነውን እንመልከት፤ ሰንት ወታደር ነው ያለቀው። የስንቱ ሬሳ ነው ነዳጅ እየተርከፈከፈበት የተቃጠለው። ስንቱ ነው ሬሳው በአደባባይ የተጎተተው። ከእነዚህ ወታደሮች መሃከል ጥቂቶቹ በመለስ ትእዛዝ ከምርጫ 97 በኋላ ወንድመቻቸውንና እህቶቻቸውን ጨፍጭፈው ሊሆን ይችላል። መለስ እንደዛ አይነት ታዛዥ አገልጋዮቹን ወደ ሶማሊያ ልኮ ለእልቂት ይዳርጋል ብዬ አላስብም። ይሄኔ እነሱ ከፍተኛ አበል በሚከፈልበት የተባበሩት መንግስታት የሰላም ጥበቃ ላይ በአሜሪካን ዶላር እተከፈላቸው ወደሚሰሩበት ሃገር ተልከው ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ከእዚህ ምሬት ተነስተን የአገዛዙ ወታደሮች ናቸው ብለን ልናፈው ከማንችልበት ደረጃ የደረሰ ግፍ እየተፈጸመባቸው ነው። የወንደሞቻችንና የእህቶቻችን ሬሳ ትረጉም በሌለው ጦርነት፣ ውሎ አድሮ ለሃገራችን ውርደትና የረጅም ግዜ መዘዝ ይዞ በሚካሄድ የሶማሌ ጦርነት ውስጥ ማግዶ፣ ሁላችም እያሰቀቀ የሚኖር እብሪተኛ በነገሰበት ሃገር ምን አይነት ተጨማሪ ቀውስ ነው ግንቦት 7 እነዚህ ግፈኞች በጋራ ታግለን እናስወግዳቸው በማለቱ ሊመጣ የሚችለው። ግንቦት 7 የመረረ አቋም ከመውሰዱ በፊት እኮ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ግለቱ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ የማይመጣ የአመጽ ትግል እየተስፋፋ ነበር። ወይስ ያልካቸው ነቃፊዎቻችን ወያኔ የሚለውን እኔ ከሄድኩ ከእዙህ የባሰ ቀውስ ይደርሳል የሚለውን ፕሮፓጋንዳ እየደገሙልን ነው። ወይስ እነሱ በሚኖሩበት አካባቢ እኛ የምንለው ቀውስ የለም። እኛ ከእዚህ የባሰ ቀውስ አይመጣም። ከእዚህ የባሰ ቀውስ የሚመጣው መለስና እብሪተኞቹን ለጥጋባቸው የሚመጥን እልህ፣ ቁርጠኛነት የማናሳያቸው .፤ በሃገራችን ላይ የሰፈነው አደጋ ለማስወገድ ተባብረን መቆም ካልቻልን ብቻ ነው። በሚገባቸውም መንገድ እንደምንታገላቸው ግልጽ ካላደረግንና ስንታገላቸውም ካልታየን ብቻ ነው። በተለይ ሁሉንም ተቃዋሚዎች ለሚያስተባብር ሁሉንም ሊያስማማ በሚችል አጀንዳ ላይ ለማሰባሰብ የሚደረግውን ጥረት በስራ ለመተርጎም ከጣርን ብለን እናምናለን ለእዚህም ተግተን እየሰራን ነው። በቅርብ ግዜ ውስጥ መለስና አጫፋሪዎቹ የሚተማመኑበትን ከፋፍሎ የመግዛት እርስ በርሳችሁ እንደትጫረሱ እናደርጋለን የሚል ማስፈራረያ ከንቱ እናደርገዋለን።

ጋዜጠኛ ——- ታዲያ ይህ በትግል ስልት ላይ ያለ የአመለካት ልዩነት፤ ቀደም ብለው እርስዎ ሁሉንም ለማስተባበር በሚችል አጀንዳ ዙሪያ ተቃዋሚዎች በአንድነት ዙሪያ እንዲሰሩ ላደረጉት ጥሪ እንቅፋት አይሆንም? አንዳንዶቹ የአገዛዙን እውቅና ባገኘ ፈቃድ ተንቀሳቀስን ዴሞክራሲን ታግለን እናመጣለን ይቻላል ብለን እናምናለን ካሉ፤ እናንተ ድግሞ አገዛዙ ፍጹም አማባገነናዊ ነውና ፋቃድም እውቅናም አንጠይቅም በመሰለን ዘዴ ሁሉ እንታገለዋለን ካለችሁ ይህ ልዩነት ቸግር አያመጣም ወይ።

አቶ አንዳርጋቸው——- በግንቦት7 አመለካከት አያመጣም ባዮች ነን።ችግር እንዳይኖር ግን በሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች መሃከል መግባባት ሊደረስባቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ። በቅድሚያ በሃገራችን ህዝብ የስልጣን ባለቤት እንዳይሆን እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች መጥረግ፣ በቦታቸው ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎችም የህብረተሰቡ የተደራጁ አካላትና ህዝብ የተሳተፉበት ሁሉንም በእኩልነት የሚያስተናግዱ ተቋማት ምስረታ በላይ የላቀ ሃገራዊ የፖለቲካ አጀንዳ ዛሬ በሃገራችን አለ ወይ። እኛ የለም ብለናል። ሌሎቹም ተቃዋሚዎች በእዚህ ላይ ግልጽና የማያሻማ መለስ ሲሰጡ አላየንም። የትግል ስልትና የአደረጃጀት ስልት ላይ ሳይሆን ችግሩ እዚህ ላይ ነው። ይህንን እንዲመልሱ እንሻለን። በእዚህ ላይ የጋራ አቋም ካለን አደረጃጀታችን ችግር አያመጣም። ህጋዊ በሆነ መንገድ የአገዛዝ ስርአቱን ፈቃድ ያገኙት በአንድ አይነት የትብብር መድረክ ሊተባበሩ ይችላሉ። እኛ ደግሞ ስርአቱን በምንም መንገድ አናምን፤ በሚፈቅደው መድረክ ትግል ማድረግ አይቻልም ከሚሉ ነገር ከላይ ያስቀመጥኩትን አጀናዳ አጀንዳቸው አድርገው ከሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ጋር አቅማችንን እናስተባብራለን።

ብቸኛ ነው ብለን ያስቀመጥነው ሃገራዊ አጀንዳ አንግበው አሁን ባለው አፋኝ ሃገራዊ ሁኔታ የያዝነው የትግል ስልትና አደረጃጀት መታገል ይቻላል ካሉ የሚያጣላን ነገር የለም። ያዋጣል ካላችሁ ቀጥሉ ነው የምንለው። በእዚህ ትግል የምንፈለገውን መሰረታዊ ለውጥ ካመጣችሁ እሰየው። እኛንም ሌላውንም ብዙ መስወእትንት ከሚጠይቅ መራረ ትግል ገላገላችሁን ነው የምንላቸው። እኛን ለመተቸት ስትነሱ ግን ሌላው ቢቀር በሁሉም መስኩ አቋማችሁን እንደኛ ግልጽ አድርጉ ነው የምንለው። በተረፈ ሁላችንም በየጎራችን ሆነን መስማማት የሚገባን፤ ከመስማማት ውጭ ማድረግ የምንችለው ነገር የለም። ይህም ስምመምት በውስጠ ታዋቂ ካልሆነ በመግለጫ የሚወጣ አይደለም። ከመንግስት እውቅና አግኘተው የሚንቀሳሱትም ሆኑ ሌሎቻችንም ህዘቡን በአንድ መሰረታዊ ጉዳይ ዙሪያ እንዲደግፈን እንማጸነው። ሁላችንም ለአንድ አለማ እንደቆምን እስካወቀ ድረስ ህዝቡ በራሱ ሲያሻው ሁሉንም መደገፍ የሚችልበትን ዘዴ አያጣም፤ ወይም ህዝብ ያዋጣኛል ብሎ አንዱን ለይቶ ለመደገፍ ዘዴ አያጣም። የፖለቲካ ግባችን አንድ እስከሆነ ድረስ የትግል ዘዴያችንና አደረጃጀታችን የሚያጣላ አይመስለኝም።

ጋዜጠኛ——-የሚሉት ይገባኛል ነገር ግን ጉዳዩ እንደሚሉት ቀላል አይደለም። አመጽን የሚቃወሙ ሃይሎች የሚሉት በአመጽ ከሚመጣ ማናቸውም ሃይል በተለይ ዴሞክራሲንና ነጻነትን ማግኘት አይቻልም። በደርግም በወያኔ/ኢህዴግም ግዜ የታየው ይህ ነው። የሚባለው ግንቦት 7 ከመሳሰሉ ሃይሎች ጋር በውስጠ ታዋቂም ሆነ በሌለ መንገድ አብሮ መስራት አይገባም። እንዲያውም አካሄዳቸውን ካሁኑ በመኮነን ማስቆም አለብን የሚል አመለካከት ያላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች አሉ። ይህ ሁኔታውን የበለጠ አያከብደውም። አይወሳሰበውም።

አቶ አንዳርጋቸው———-አዎን ይወሳሰበዋል። የሚወሳሰበው ግን እውነት ስለሆነ አይደለም። የሚወሳሰበው አሁን በኢትዮጵያ ሁኔታ በአመጽና በሃይል ለብቻዬ ስልጣን ልያዝ የሚል የፖለቲካ ንቅናቄ እንዳለ አደርጎ የውሸት መንደርደሪያ ስለሚያቀርብ ብቻ

**ወደ ገጽ4 ዞሯል**

ቃለ - ምልልስ ከገጽ 3 የዞረ

ነው። ይህንን ከመግለጼ በፊት በጠቅላላ አባባሉ ላይ ያለውን ምሁራዊ ድክመት ልግለጽ። እውን ነው በሃገራችን በአመጽ ስልጣን ላይ የወጣ፣ እስካሁን በሃገራችን ዴሞክራሲ ሲያመጣ የህዝብ መብት ሲያስከበር አይተን አናውቅም።

በሌሎች የአለማችን ክፍሎች ግን በአመጽ አንድን ግፈኛ መንግስት አስወግደው ዴሞክራሲን ለህዝባቸው ማላባስ የቻሉ በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ታይተዋል። በአፍሪካችን ደግሞ በሰላምና በውድድር ስልጣን ከያዙ በኋላ በሌላ ውድድር ሲሸነፉ ከስልጣን አልወርድም ብለው በአምባገነንነት የሚቀጥሉ መሪዎችና ድርጅቶም እናያለን። ባጭሩ በሰላም ስለመጣ ዴሞክራሲን ይገነባል፣ በአመጽ ስለመጣ አምባገነን ይሆናል የሚለው ድፍን ክርክር ምሁራዊ ወሃ አይቋጥርም ለማለት ነው። እግሬ መንገዴን በሰላም የመጣውን ሃይል ላስገደደ ህዝብ የተሻለ እድል እንዳለው ግን አይካድም። መለስ ዜናዊ እኮ ትንሽ ሃገር ፍቅርና ያለውና ትንሽ አብርሆት የቀመሰ መሪ ቢሆን ኖሮ፤ በምርጫ 97 ህዝብ ለሰጠው ውሳኔ ተገዥ ሆኖ ስልጣኑን በክብር ለህዝብ ማስረከብ ይችል ነበር። የ1997 የዴሞክራሲ ብልጭታ የወደመው የሃገራችን ህዝብ ለዴሞክራሲ ዝግጁ ስላልሆነ እኮ አይደለም። የአገዛዙ ባለስልጣናት ከህዝብ ብስለትና እውቀት ጋር መራመድ ያልቻሉ ደንቆሮዎችና ራሳቸውን ከህዝብና ከሃገር የሚያስቀድሙ ስግብግቦች ስለሆኑ ብቻ ነው። እንደሚባለው ችግራቸው በጠመንጃ ሃይል ስልጣን የወጡ በመሆናቸው ብቻ አይደለም። በጠመንጃ ሃይል ስልጣን ላይ የወጡ በሌሎች ሃገሮች የዴሞክራሲ ስርአት ገንብተው አሳይተውናል። በአለም ላይ ብዙ ምሳሌዎች አሉ። እዚሁ አፍሪቃ ወስጥ እኮ የነጋና ዴሞክራሲ ምንም ማስመሰል በሌለበት የወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት የተጀመረ ነው።

ወደ ዋነኛው ቁም ነገር ስንመለስ የራሳችንን ጥያቄ ማቅረብ አለብን። ማነው ዛሬ በኢትዮጵያ የጠመንጃ ትግል ለብቻዬ አካሂጄ ስልጣን እይዛለሁ፤ ከያዝኩ በኋላ ዴሞክራሲና ነጻነት አድላለሁ ብሎ እንደ ቀድሞዎቹ ነጻ አውጪዎች እየተንቀሳቀሰ ያለው? ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ስልጣን ቢይዙ ለህዝብ ምን ሊሰሩ እንደሚፈልጉ በፕሮግራማቸው ይቅረጹ እንጂ በጠመንጃ ሃይል ስልጣን ለብቻዬ ይዤ ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አስተዳድራለሁ ወይም ዴሚክራሰ አሰፍናለሁ የሚል ሃይል ዛሬ የለም። ያ ዘመን ከነጻ አውጪዎቹ ዘመን ጋር አብቅቷል። በሃይል የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች እሳካሁን ደጋግመው ያቀረቡት ሃሳብ ሁሉም የፖለቲካ ድርጀቶች፣ የህብረተሰባችን ወኪሎች በጋራ የሚመክሩበት ገባኤ እንዲጠራና እንዴት ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር እንደሚደረግ እንምክር ነው እያሉን ያለው።

በግንቦት ሰባት በኩልማ ስልጣን የመያዝ አጀንዳ በፕሮግራሙ አልሰፈረም። ሁሉንም የትግል ስልት ተጠቅሞ ሊፈጥር የሚፈልገው ሁኔታ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ ባጋራ የሚመክሩበት፤ ህዘብን የስልጣን ባለቤት የሚሆንበትን የጋራ መድረክ ለመፍጠር እንደሆነ ግልጽ አድርጓል። ይህንን ግልጽ አድርጎ ገና ከመጀመሪያው፣ ከሁሉም ድርጅቶች በቀጥታም ይሆን በተዘዋዋሪ በሚደረግ የትግል ትብብር ህዘብን የሰልጣን ባለቤት አናድርግ ብሎ አበላቶን፣ ህዝብ በሚያስተምርበት ወቅት፤ግንቦት ሰባትንና ሌሎቹ ሃይሎች በጠምንጃ ሃይል ህዝብንና ሌሎችን የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ጎን አድርገው ስልጣን ሊይዙ ነው የሚል ማስፈራሪያ በፖለቲካ መስኩ የሚሉት ነገር ከሌላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች የሚሰነዘር ባዶ ክስ ነው። ህዝብን ጭራቅ ሊመጣበህ ነው በሚል ማስፈራሪያ አምሮ እንዳይነሳ፣ አማራጭ እንደሌለው፣ ይህንን በሚሉት ሃይሎች ስር ተገዥ እንዲሆን ለማድረግ ይመስለናል። ህዝብ ደግሞ የወያኔ ተገዥ ከመሆን አልፎ፣ ሌሎች ግለሰቦችና ቡድኖች ለሚያሰራጩት የሽብርና ወሬ ተገዢ እንደማይሆን እናውቃለን። ህዘብና ሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች ቢሆኑስ፤ ከአሁን በኋላ ሰልጣን ይዤ መብታችሁን አስከብራለሁ ለሚል ባለጠምንጃ በጭፍን ድጋፍ ይሰጣሉ ብሎ ማሰብ ህዝብንም መናቅ ይሆናል። በሃገር ቤትም ሆነ በውጭ ሃገር የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ግንቦት ሰባትን የሚደግፈው ጉልበት ስላለው፣ ወያኔን በአመጽም ቢሆን ልናስወግደው ይገባል ስላልን አይደለም። ድጋፍ የምናገኘው ሁሉንም የፖለቲካ ድርጀቶች በማስተባበር የመለስ ዜናዊን አምባገንናዊ አገዛዝ በሃገራችን የመጨረሻው አገዛዝ ለማድረግ በህዝብ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ መንግስታዊ ስርአት መገንባት ያስፈልጋል፣ የወቅቱ የፖለቲካ አጀንዳ ስልጣን መያዝ ሳይሆን ህዘብን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ በጋራ መንገዱን መጥረግ ነው ስላልን ብቻ ነው።

በአመጽ ስልጣን ሊይዙ፣ ህዝብ ከላቀ በኋላ በአውሮፓላን ተጭነው ምኒሊክ ቤተ መንግስት ውስጥ ገብተው፣ በህዝብ ላይ ሌላ የመከራ ዘመን ሊያዘንቡ፤ በአውሮፓ በአሜሪካ ያደቡ ጭራቆች እንዳሉ አድርገው አንዳንዶቹ የሚያቀርቡት ተራ ወሬ ዛሬ ሃገራችን ያለችበትን ሁኔታ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ስለስልጣን ባለቤትነቱ ያለው ግንዛቤ፣ የሃገራችን ፖለቲካ ችግር በአንድ አምባገንናዊ ግለሰብ ወይም ቡድን ሊቃላል የማይችል፣ ሁሉንም የፖለቲካ ተዋንያኖች፣ ድርጅቶች፣ ሲቪል ማህበረሰቡን፣ የሙያ፣ የሃይማኖትና ሌሎችም ሀገራዊ ተቋሞች በማካተት ብቻ እንደሚቃልል ልክ እንደ መለስ ዜናዊ ያልገባቸው የተናንት ሰዎች ብቻ ናቸው። ሰላማዊ የህዝብ አምቢተኛነትና የአመጽ ትግል መለስና ጭፍሮቹን አስገድዶ ወደ ድርድር ያመጣቸዋል ወይም ያስወግዳቸዋል። ይህ ድርድር ደግሞ ከመጀመሪያውም ሁሉን እንዲያሳትፍ ተደርጎ የተቀረጸ በመሆኑ፤በአመጽ ሃይል ማንም ለብቻው ስልጣን ላይ ፊጥ ሊል አይችልም። ግንቦት ሰባትም የቆመውም ይህ እንዳይሆን ነው።

ጋዜጠኛ ———እንዳሉት ያለንበት ሃገራዊም ሆነ አለምአቀፋዊ ሁኔታ የአንድን ድርጅት ብቸኛ አምባገንናዊ ስልጣን የማይፈቅድ ነው የሚለውን እንቅበል። የመለስ አገዛዝ ኖረበት አልኖረበትም እርቅ፣ ድርድር፣ ስምምነት ሳይደረግ ፈቃቶ ማለት አይቻልም። ነገር ግን በእዚህ በሃይል መንገድ ከተጓዝን መለስ ጠመንጃውም፣ ፈንጅውም፣ ገንዘቡ በእጁ ስላለው ሃገር ያጠፋል፤ እናስወግደሃለን እያልን ባናስበረግገው ይሻላል። ሃይል ቃል ሳንጠቀም በማባባል። ከስልጣን ቢወርዱ በሰላም የዘረፉትን እየበሉ እንደሚኖሩ ቃል በመግባት፤ በሰሩት ወንጀል እንደማይጠየቁ በማግባባት ብቻ ነው መሄጃው። እንዲህ አድርገን ቀስ ብለን እንገላገላቸዋለን የሚሉ አሉ። ይህንን እንዴት ያዩታል።

አቶ አንዳርጋቸው——-አገረ ያጠፋሉ የሚለውን አስተያየት ቀደም ብዬ መልሸዋለሁ። ይህንን ልተወው። እንዲህ አይነት አስተያየት የሚሰጡ ሰዎች ምን አድርጉ ነው የሚሉን። ፈጣሪ የሰጠንን አያት ቅድማያቶቻችን ሃገራችንን የወረረ ጠላት ሲያገላግሉ ሳይሆን፤ ከጠላት ጋር ሲተናነቁ ያቆዩልን ነጻነት መብትና ሃገር ለመለስ ዜናዊ አይነቱና የጸረ ኢትዮጵያ የዛር ውላጅ ለሚጨፍርባቸው ሃይሎች አስረክበን አንገታችንን ደፍተን እንኑር። አጼ ሃይለ ስላሴም የጸሃዩ ንጉስ ሁሉም አይነት መሳሪያ ነበራቸው። መንግስቱም ሃይለማሪያምም በአፍሪካ ተወዳደሪ ያልነበረው ነበረው። ሁለቱም መንግስታት ጸረ -ሃገርና ህዝብ ከሆነው የወያኔ ኢህአዴግ አገዛዝ የተሻለ ተቀባይነት ነበራቸው። ውሎ አድሮ ግን ቀናቸው ሲደርስ ሄደዋል። የመለስ አገዛዝ ቀኑ ካለፈ ሰንብቷል። እንዴት ሆኖ ነው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተወዳዳሪ በማይገኝለት ንቀትና ጥላቻ እየታየ በተባባረ ሕዝብ ፊት የሚቆመው። መለስ አብሪትና ቅንጦት ባወረው የገዘዎች የተለመደ ህሊና ያለበትን ተቦርቡሮ ያለቀ አገዛዙን ማየት አይችል ይሆናል። በእኛ እምነት በአነስተኛ የህይወትና የንብረት ኪሳራ በአጭር ግዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሰፍረው ደሙን የሚመጡትን መዥገሮች ማንሳት እንችላለን። ይህን የሚወስነው በቀቶኛል ብሎ ተንገፍግፎ የተነሳው የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ነው።

ጋዜጠኛ — አቶ አንዳርጋቸው ቃለ- ምልልሳችን እያጠናቀቅን ስለሆነ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልእክት ካለ።

አቶ አንዳርጋቸው——አመሰግናለሁ እስካሁን በተደረገው ቃለ-ምልልስ ግንቦት 7 ምን አላማ አንግቦ እንደተናሳ ግልጽ አድርጊያለሁ። በጥሞና ላዳመጠ የግንቦት 7 አላማ ወገንተኛ ያልሆነ ሁሉንም ዜጋና የፖለቲካ ድርጅቶች በእኩልነት ሊስተናገዱ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ስለሆነ በሃገራችን፤ ህዝብ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ሆኖ ማየት የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ የግንቦት7 ንቅናቄን ሊቀላቀሉ ሊደግፉ ይገባል እላለሁ። ለእዚህ ጥሪ አቀርባለሁ። ይህ የድጋፍ ጥሪ ሌሎችንም የፖለቲካ ድርጅቶች ከሚደግፉ አባላትና ደጋፊዎች፤ ከራሳቸውም ከሌሎቹም የፖለቲካ ድርጅቶች መምጣት ይገባዋል እላለሁ። ለእዚህም በቂ ምክንያት አለኝ።

የግንቦት ሰባት አለማ፣ አላማቸው በነጻ ውድድር በህዝብ ምርጫ ስልጣን ለመያዝ ከሆኑ ድርጅቶች የተለየ ነው ብዬ አላስብም። በተለይ ደግሞ በተለያዩ ታሪካዊና ወቅታዊ አጋጣሚ የወያኔ/ኢህአዴግ አባላት በመሆን መላው ህልውናቸውን ከመለስ አገዛዝ ጋር አቆራኝተው፣ ይህ አገዛዝ ሲያበቃ ህይወት የሚያበቃ የሚመስላቸው ወገኖቻችንን ከእዚህ ጭንቀት የምትገላገሉት፤ የስራና የኑሮ ዋስትናችሁ የሚጠበቀው፤ ህዝብ ለነጻነትና ለመብቱ የሚደረገው ትግል አጋር ስትሆን ብቻ ነው እላችኋለሁ። ማለፉ ከማይቀረው ሰው በላ አገዛዝ ጋር ተጣብቃቸሁ፣ የመለስ ግፈኛ አገዛዝ ካደሬዎችና ወታደሮች እየተባላችሁ፣ ስማችሁንና ጥቅማችሁን ለዘላለሙ ከማጥፋት፤ ከአሁኑ እናንተም እንደ ወገናችሁ መለስን በቃን ልትሉት ይገባል እላላሁ።በቀቶናል የአንተ መሳሪያ አንሆንም ልትሉት ይገባል። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ አላማ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ እናንተንም ጨምሮ የመብት፣ የነጻነት፣ የስራና የመኖር ዋስትናችን ከዜግነት መብታችን የሚመነጭ እንጂ የመለስ ባርያ ስለሆንን እንደ እርጥባን እየቆነጠረ በበጎ ፈቃዱ የሚሠጠን እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ነው። ስለሆነም እናንተም እንደ ሌሎች ወገኖቻችሁ ግንቦት ሰባትን አግዙ። በአንድነት ከቆምን የሁላቸንንም የመከራ ግዜ ማሳጠር እንችላለን።

**ለእርስዎ፤ ለአንተም፤ለአንችም ለእኔም!**

**ኢትዮጵያን ለእኛ ለማስተላለፍ ቀደምቶቻችን የከፈሉትን ግዙፍ መስዋእትነት እናስበው፡፡**

**ዛሬ በሃገራችን ላይ የነገሱት ከሃዲዎች ይህንን መስዋእትነት ሲያረክሱ፣ ትውልድ በደሙ አጥሮ ያስረከበንን ሃገር ሲያፈርሱ በዝምታ ማየታችን ይቁም፡፡**

**በቃ በቃ እንበል! እንሰባሰብ! እንነሳ!**